Ricin Amharic

# ሪሲን



*የጉሎ ፍሬዎች*

## ሪሲን ምንድን ነው?

ሪሲን የመርዝ ዓይነት ነው። ጉሎ ዘይት ለመሥራት ከሚጠቀሙበት ከጉሎ ፍሬ የሚመጣ ነው። እንደ ፈሳሽ፣ ዱቄት ወይም ክሪስታል ሆኖ ሊሠራ ይችላል።
አንድ ሰው እንዳጋጣሚ በሪሲን መመረዝ መቻሉ አዳጋች ነው። ሰው ሊመረዝ የሚችለው ሪሲንን አውቀው እንደ ጦር መሣርያ ከተጠቀሙት ብቻ ነው።

ሪሲንን ምግብ ውስጥ ወይም ውሃ ውስጥ በመጨመር ሰውን መመረዝ ይቻላል። ፈሳሽ ወይም ዱቄት ሪሲን አየር ውስጥ ከተበተነና ሰዎች ከተነፈሱት ሊመረዙ ይችላሉ። ከፈሳሽ ነገር ጋር ከተበጠበጠ በቆዳ ውስጥ ወደ ሰውነት ሊገባ ይችላል - በዚህ መንገድ ግን መመረዝ መቻል ከሌሎቹ መንገዶች ሁሉ ያነሰ ነው። በመርፌ በመውጋትም አንድን ሰው መመረዝ ይቻላል።

በሪሲን መመረዝ ሊገድል ቢችልም ሁልጊዜ ግን ለሞት አያደረስም። ምልክቶቹ እንደ ሪሲኑ ብዛትና ሰው እንደተጋለጠበት መንገድ ይለያያሉ፦

- ***ውሃ ወይም ምግብ*** ውስጥ ያለ ሪሲን ኃይለኛ የምግብ መመረዝ ሕመም ዓይነት ምልክቶች ሊያመጣ ይችላል - ማስታውክንና ደም የተቀላቀለበትን ተቅማጥ ጨምሮ። ጉበትንና ኩላሊትንም ይጎዳል። መጠኑ ብዙ ከሆነ በሶስት ቀን ጊዜ ውስጥ ሊገድል ይችላል። አንድ ሚሊግራም ሪሲን ምግብ ወይም ውሃ ውስጥ ከገባ አዋቂ ሰውን ሊገድል ይችላል።
- ሪሲንን ***የሚተነፍስ*** ሰው በሶስት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሳል ይይዘዋል። በሚቀጥሉት ከ18 እስከ 24 ሰዓት ውስጥ ማቅለሽለሽ፣ ተቅማጥና ሕመሞች ይከተላሉ። መጠኑ ብዙ ከሆነ ልብና የደም ቧንቧ ላይ በሚያስከትለው ጉዳትና ሳንባ ውስጥ በሚፈጥረው ፈሳሽ ምክንያት ከ36 እስከ 72 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ሞትን ያስከትላል።
- ሪሲንን ***በመርፌ መውጋት*** የተወጋበት አካባቢ ያሉትን ጡንቻዎች ያበላሻል። ዋና የሰውነት ክፍሎች ስለሚበላሹ ብዙም ሳይቆይ ሞት ይከተላል።
- ሪሲን ***በቆዳ በኩል*** ገብቶ መመረዝ መቻሉ ለመርዙ ከመጋለጫ መንገዶች ሁሉ ያልተለመደው ነው - በዚህ መንገድ ለሞት ማድረሱም እንደሌላው አይሆንም። በዚህ መንገድ ለመጠቀም ከሌላ ፈሳሽ ጋር መበጥበጥ አለበት። ምልክቶቹ እንደተበጠበጠበት ፈሳሽና ከቆዳ ጋር ለምን ያክል ጊዜ እንደተነካካ ይለያያሉ።

## በሪሲን መመረዝ ሊታከም ይችላል?

በአሁኑ ጊዜ ሪሲንን የሚያፈርስ መድሃኒት ባይኖርም የሪሲን መመረዝ ምልክቶች መታከም ይችላሉ። ሕክምናው በሽተኛው ለመርዙ እንደተጋለጠበት መንገድ ቢለያይም ለመተንፈስ እርዳታ መስጠትና በደም ሥር የሚሰጡ ፈሳሾችንና መድሃኒቶችን ሊጨምር ይችላል። ከአምስት ቀን በላይ የሚቆዩ ሰዎች የመዳን ዕድላቸው ጥሩ ነው።

## ሰዎች ከሪሲን መርዝ መከላከል ይችላሉ?

በአሁኑ ጊዜ ከሪሲን ተጸዕኖዎች አስቀድሞ የመከላከያ መንገድ የለም። ክትባት የመሥራት ዕድሉ እየተጠና ነው።

## የሪሲን መርዝ ከሌላ ሰው ሊይዝ ይችላል?

አይችልም። ሪሲን የመርዝ ዓይነት ነው። ሕይወት ባለው ሕዋሳት የሚመጣ ስላልሆነ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም።

## ሪሲን የሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል የሚባለው ለምንድን ነው?

ሪሲን የሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ሊሆን እንደሚችል አንድ ክፍለ ዘመን ያክል ለሚሆን ጊዜ ተጠንቷል። አሜሪካ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ሲያጠናው ነበር፣ የእንግሊዝና የአሜሪካ ሳይንቲስቶች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የሪሲን ቦምብ ሠርተው ሞክረዋል።

በ1990 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ በሰሜን ምዕራብ ሚኔሶታ ውስጥ አንድ የሚሊሻ ቡድን ሪሲንን በሕግ አስከባሪ ሠራተኞች ላይ ለመጠቀም አሴረው ነበር። ኢራቅ ሪሲንን እንደ መሣሪያ ለመጠቀም እንደሠራች ይታመናል። አልቃይዳም ከሪሲን አጠቃቀም ጋር የሚያገናኝ ማስረጃ ተገኝቷል። በ1978ዓ.ም. ለንደን

Communications Office
625 North Robert Street/Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-4989
www.health.state.mn.us

ውስጥ የመርፌ ሪሲን ተጠቅመው አንድ የቡልጋሪያን ተቃዋሚ የአውቶቡስ መቆሚያ ጋር ገድለውታል።

ሪሲን እንደ ሽብር መፍጠሪያ የጦር መሣሪያ ተጠቅሞ አይታወቅም። ሪሲንን አየር ውስጥ በትልቁ መልቀቅ መቻሉም የተረጋገጠ አይደለም። ከሁሉ በላይ ሊሆን የሚችለው ሪሲንን የገለለ ቦታ ላይ መጠቀም ነው - ለምሳሌ ሰብዌይ ላይ፣ አውቶቡስ ውስጥ ወይም ሱቅ ውስጥ።

ሪሲን የሽብር ጦር መሣሪያ ይሆናል ተብሎ የሚታመነው በእነዚህ ምክንያቶች ነው፦

- ለመሥራት ርካሽና ቀላል ነው
- ክትባትና ሕክምና የለውም
- በጣም መርዘኛና የብዙ ሰው ሞት የሚያስከትል ነው

## ለሪሲን የተጋለጥኩ ከመሰለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

ለሪሲን የተጋለጡ ከመሰልዎት ዶክተርዎን በአስቸኳይ ያነጋግሩ። በአካባቢዎ ጥርጣሬ የሚያሳድር እንቅስቃሴ ካዩ - ማለትም እንደ ሪሲን ዓይነት ኬሚካልን እንደ ጦር መሣሪያ ለመጠቀም የሚሞክር ካዩ - በአካባቢዎ ለሚገኘው የሕግ አስከባሪ ድርጅት ያሳውቁ።